**ለ** ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ

**ጉዳዩ** ፣ ከኢትዮጵያ ተቆርሶ ለሱዳን ስለተሰጠው መሬት

**ቀን** ፣ ጥር 10 ቀን 2000 ዓ.ም. ( January 19, 2008 )

ለአለፉት 6 ወራት ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር በረጅሙ በሚያዋስናት ሰሜን ምዕራብ የግዛት ድንበር ለም መሬት ለሱዳን መሰጠቱን አንዳንድ የዜና አውታሮች መዘገባቸው በአሁኑ ጊዜ ለብዙ ኢትዮጵያውያን አዲስ ጉዳይ አይደለም። በዚህም የተነሳ በዚሁ የሀገራችን ክልል ለዘመናት የኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከእርሻ መሬታቸውና ከመንደሮቻቸው ተፈናቅለው ለከፍተኛ ችግርና ስደት ተዳርገው ይገኛሉ።

ይህ ከፍተኛ የሀገር ጉዳይ እጅግ ያሳሰበን ኢትዮጵያውያን በሥልጣን ላይ ያለውን የኢሕአዴግ መንግሥት ለሚመሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በጉዳዩ ላይ አውንታዊ ሆነ አሉታዊ መልስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽና ትክክለኛ መረጃ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ግልጽ ደብዳቤ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ነሐሴ 2 ቀን 1999 ዓ.ም. ( August 8, 2007 ) በመጻፍ በተለያዩ ድሕረ-ገጾች ላይ እንዲወጣ ማድረጋችን የሚታወስ ነው።

ይሁን እንጂ ፤ እስከ አሁን ድረስ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሆኑም ማናቸም የኢሕአዴግ መንግሥት ባለሥልጣናት ጉዳዩን በሚመለከት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድም የተነፈሱት ነገር የለም። በዚህ ፋንታ ፤ ጠቅላይ ሚኒሰትር መለስ ዜናዊ ወደ ሱዳን ርዕሰ ከተማ ካርቱም በመዝለቅ ከሱዳን መሪ ጋር ውይይት ማድረጋቸውና እርሳቸውን አጅበው የሄዱ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ደግሞ ከሱዳን አቻዎቻቸው ጋር በድንበሩ አካባቢ ስብሰባዎች በማድረግ ርክክቡን እያከናወኑ መሆናቸውን ከሱዳን ዜና አውታሮች ለመረዳት ተችሏል።

ከዚህም ተያይዞ የደረሱን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ደግሞ ፤ ሱዳን እየተካለለችው ያለው የመሬት ርዝመት 1600 ኪሎ ሜትር የሚሆን ሲሆን ስፋቱ ደግሞ በብዙ ኪሎ ሜትር የሚለካና ዋናውን የአትባራ ወንዝ ወደ ሱዳን ያካተተ ነው።

ሱዳን በየጊዜው ያነሳችው የይገባኛል የድንበር ጥያቄ በየዘመኑ ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ የነበሩ መንግሥታት ምላሽ እንደሰጡበት የታሪክ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። በአፄ ምኒሊክ መንግሥት ጊዜ በወቅቱ ሱዳንን ይገዙ የነበሩት ተስፋፊ የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች በጫሩት ተንኮል የተነሳ በዘመኑ ሁለቱ መንግሥታት ተነጋግረው እልባት የሰጡት ጉዳይ ነበር። በአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጊዜም በወቅቱ የነበረው ፓርላማ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶበት ነበር።

በወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት ዘመን ደግሞ ሱዳን የይገባኛል ጥያቄ ስታቀርብ ፤ ጉዳዩን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት ለመስጠት 6 ከፍተኛ ኢትዮጵያውያን ምሑራን ያቀፈ የጥናት ኮሚቴ በደርግ ተሰይሞ ነበር። እነዚህ 6 የጥናት ኮሚቴ አባላት ፣ 1ኛ/ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም 2ኛ/ ዶ/ር መርዕድ ወልደ አረጋይ 3ኛ/ ዶ/ር ታደሰ ታምራት 4ኛ/ ፕሮፌሰር ብርሃኑ አበበ 5ኛ/ ዶ/ር ክንፈርግብ ዘለቀ እና 6ኛ/ ዲን ወርቁ ተፈራ ነበሩ። ይህ ከፍተኛ ምሑራንን ያሰባሰበ ኮሚቴ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገሮች በመዘዋወር ብዙ ሰነዶችንና ካርታዎችን መርምሮና ዓለም-አቀፍ ስምምነቶችንና ውሎችን አጥንቶ መሬቱ የኢትዮጵያ ይዞታ መሆኑን በማያዳግም ሁኔታ የሚያረጋግጥ በበርካታ ካርታዎች የተደገፈ

ጥናታዊ ሰነድ ለድርግና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ዓለም-አቀፍ ድርጅቶች አቅርቦ የጥናቱ ሰነድ ለመጨረሻ ጊዜ የሱዳንን የድንበር ጥያቄ በማያሻማ ሁኔታ ዘግቶት ነበር።

እጅግ በጣም የሚያስገርመው ግን ፤ በሥልጣን ላይ ያለው የኢሕአዴግ መንግሥት ይህ ታሪካዊ የጥናት ሰነድ በእጁ እያለ ነው ፤ የሞተውን የድንበር ጉዳይ ነፍስ ዘርቶ የሀገራችንን ለም መሬት ለሱዳን መንግሥት ገፀ በረከት ያቀረበው።

ስለዚህ ይህ ፀረ-ኢትዮጵያ የኢሕአዴግ መንግሥት የሀገራችንን አካል የሆነውን የሰሜን ምዕራብ ድንበር የሚገኘውን ሰፊ ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጥብቅ የሚቃወመውና የማይቀበለው ከመሆኑም በላይ ወደፊትም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያሰጠብቅ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ሲመጣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተሸሽጎ በድብቅ የተደረገውን ይህን የድንበር ስምምነት በምንም መልኩ እንደማይቀበለው ፣ እንደማያከብረውና በግፍ የተወሰደውን መሬቱን እንደሚያስመልስ ለማስገንዘብ እንዲቻል ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ዓለም-አቀፍ ተቋማት የተቃውሞና የአቤቱታ ጽሑፍ ( Petition ) ማዘጋጀት እንዳለብን ሀገራዊና ታሪካዊ ግዴታችን ያሰገድደናል። ስለሆነም ፥

1ኛ/ የእነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም የተሟላ የጥናት ጽሑፍ ፤

2ኛ/ ካርታዎችና ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች ፤

ያላችሁና ማግኘት የምትችሉ ሀገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፥

* በፋክስ ቁጥር ( Fax Number ) 404-880-6195 ብትልኩል ወይም ደግሞ

* በሚከተለው ኢሜል አድራሻ ( E-mail ) Leethiopia@yahoo.com ልታገኙን የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ